**SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN POLITICAL PRISONERS – CANADA (SOCEPP-CAN)**
**የኢትዮጵያ ፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ በካናዳ**
**P. O. BOX 413 STATION E, TORONTO, ON. M6H 4E3 CANADA.**
**Email: socepp.can@sympatico.ca**

May 12, 2008

## የግንቦት 07፣ 2005 ትዝታዎች በወርሃ-ግንቦት ሲዘከሩ፤

የኢትዮጵያ ፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ - ካናዳ)፤ ግንቦት 2005 ን በዛሬው ግንቦት ላይ ሆኖ የሚዘክረው በማሌሊት/ኢሕአዴግ የሥልጣን ዘመን በግፍ የተጨፈጨፉትን፤ ከየቦታው ታግተው ደብዛቸው የጠፋውን፤ በተወለዱባት አገር የመኖር መብታቸውን ተነፍገው በየጎረቤት አገሩ በመሰደድ በዕንግልት ላይ ያሉትንና አሁንም ቀጣይ አሰከፌ የመብት ረገጣ እየደረሰባቸው የሚገኙትን ወገኖቻችን አሰመልክቶ የሚሰማውን ጥልቅ ኃዘን እየገለጸ ነው።

ማሌሊት/ኢሕአዴግ አለም አቀፍ ሕግጋትን በመጣሰ ካሁን በፊት በተለያዩ የሀገሪቱ ቦታወች አንዳደረሰው ሁሉ አሁንም በአኘዋክ ብሔረሰብና በኦጋዴን ወገኖቻችን ላይ አያደረሰ የሚገኘውን ዘግናኝ የሰብዓዊ መብት ረገጣ በአንክሮ እያስታወስን ነው።

ግንቦት 2005ና የቀጠሉት ጥቂት ወራት፤ በዜና አውታሮች በግልጽ እንደተዘገበው፤ ከምርጫው ጋር ተያይዞ የዴሞክራሲ ፈለግን ለማምጣት በሰላማዊ መንገድ የታገሉ 193 ሰማዕታት በግፍ የተገደሉበት፤ ወደ ሃምሳ ሺ የሚደርሱ የተቃዋሚ ድርጅቶች አባላትና ደጋፊዎች፤ ነጻ ጋዜጠኞች፤ የሞያ መኅበራት መሪዎች፤ ተማሪዎች፤ አስተማሪዎች ወ.ዘ.ተ፤ በየእስርቤቱ ታጉረው ለብዙ ወራትና ዓመታት ያለፍትህ እንዲማቅቁ የተደረገበት፤ በሂደትም የሕዝብ ድምጽ የተሠረቀበትና ሥልጣኑም በጠመንጃ ታግቶ ለማለሊት/ኢ.ሕአዴግ የተቸረበት ወቅት ነበር”;፤

ይህን ሀቅ ሰንቃኝ ባንድ በኩል የህዝቡን ለመብቱ መከበር ያለውን ቆራጥነት በሌላ በኩል ደግሞ ጭፍጨፋውንና ያላቕረጠውን የግፍ በትር በማገናዝብ ለማኅበራዊ ፍትህ፤ ለሰላምና ለዴሞክራሲ ገና ብዙ ሥራና ትግል እንደሚጠብቀን እየተገነዘብን ነው።

ዛሬም እንደትናንቱ በኢትዮጵያችን ፍትህ የለም፤ ሰላም የለም፤ መብት የለም፤ ተቃዋሚ ድርጅቶች፣ ሲቪክ ድርጅቶችም ሆኑ ነጻ ጋዜጦች ነጻ ሆነው መንቀሣቀስ አይችሉም፤ የህዝብ አንደበት እንደተለጎመ ነው፤

ይህንን አስከፊ ሁኔታ ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመለወጥ፤ የኢትዮያ ህዝብ ስብአዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብት እንዲሁም የህግ የበላይነት እንዲከበር የሚደረገው ትግል መቀጠል ይኖርባታል;

ኢፖእአኮ ካናዳም ባለፉት ዓመታት እንዳደረገው ሁሉ የፖለቲካ እስረኞችንና የሰብዓዊ መብት ጥቃተኞችን መብት ለማስከበር የሚደረገው ትግል አካል ሆኖ ይቀጥላል። የዓለምንም ህብረተሰብ፤ በተለይ ደግሞ የካናዳ የመንግሥት ባለሥልጣኖችና የሰብዓዊ መብት አስጠባቂ ድርጅቶች ስለኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብት ሁኔታ ይበልጥ እንዲገነዘቡና ተገቢውንም አርምጃ እንዲውሰዱ ጥረቱን ይቀጥላል።

**በግፍ ጥይት የወደቁትንና ታግተውም ዱካቸው የጠፋብንን ወገኖች እንዘክራቸው!!**